PANORAMA # XXII

## የትዝብት አድማስ

ሚያዚያ 17 2000 ዓም

## ቅድሚያችን ምንድን ነው?

ሀገራችን አሁን የደረሰችበትን ሁኔታና ሂደት አስመልክቶ÷ በርካታ ትንታኔዎችን ያዘሉ ጽሁፎች በየጊዜው ስለሚተላለፉ÷ እነርሱን አስመልክቶ እንደገና ማለቱ÷ አሰልቺ ሊሆን መቻሉን ተገነዝብንም አልተገነዘብን÷ጉዳዩን መላልሶ መላልሶ ማውሳቱ ግን የምናልፈው ዕዳ አልሆነልንም። የሀገራችን ችግሮች በየጊዜው እየተበራከቱና እየተባባሱ በሄዱ ቁጥር÷ እንደሁኔታው እየተከታተሉ ጉዳዮችን መግለጽ የሕዝቡን ትግል ማጠናከር በመሆኑ÷ ይህንን ከማድረግ አንቆጠብም።

በዛሪይቱ ዓለማችን ከሚኖሩት ሀገሮች ውስጥ÷ ዘርፈ ብዙና ውስብስብ ችግሮች ካሏቸው ሕዝቦች መካከል ኢትዮጵያ ሀገራችን አንዷ ነች ማለቱ÷ ጉዳዩ ጎልቶ እንዲታይ ከማድረግ በስተቀር÷ ተስፋ አስቆራጭ አባባል ነው ሊባል አይችልም። በቅድሚያ ሦስት ሀቆችን በግንባር ቀደም ማስቀመጥ እንፈልጋለን። አንደኛ እጅግ ውስብስብና ጥልቅ የሆኑ ችግሮች ያሉባት ሀገር አለችን። ሁለተኛ÷ ከብዙ የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር÷ የበለጠ ቁጥር ያለው የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል ያላት ሀገር እንዳለችን በጥናት የተደገፈ ሀቅ ነው። ነገር ግን ሀገራችን ያስተማረቻቸውን ምሁራንም ይሁን የሠለጠነውን የሰው ኃይል በሚገባ አልተጠቀመችባቸውም። ሦስተኛ÷ በተፈጥሮ ኃብትና በተስማሚ አየር ጠባይ በኩል በዓለም ካሉት ሀገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ለመሆኗ የሚያከራክር አይደለም። የተፈጥሮ ኃብቷ ግን÷ ላም አለኝ በሰማይ ከመሆን አልፎ÷ ችግሯን ልታስወግደበት አልቻለችም። ምክንያቶቹን ሁሉ መዘርዘር የሚያስፈልገን ባይሆንም÷ የሰላምና መረጋጋት አለመገኘትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አለመኖር እንደ አበይት ምክንያቶች የሚቆጠሩ ይሆናሉ። ወያኔ በሥልጣን እስካለ ድረስ ደግሞ÷ በሀገራችን ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖ÷ የዴሞክራሲ ሥርዓት የከሰታል ማለት ዘበት ነው።

እነዚህን ሀቆች ተገንዝበ፥ ሀቆችን ከሁኔታዎች ጋር አገናዝበ፥መፍትሄ ለማግኘት ካልተሞከረ፥ ዓላማችን ሁሉ የእንቧይ ካብ ሆኖ ይቀራል፡፡ የሀገሪቱን ሁኔታ በየፈርጁ አስቀምጦ፥ ሀገራዊ አጀንዳዎቹን በቅደም ተከተል አስተካክሎ፥ በጋራ በመፍትሔ ፍለጋው ሂደት ላይ መረባረብ፥ ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ነገር አይደለም፡፡ ይህን ጉዳይ ደግመን ደጋግመን ማውሳታችን፥ ወደን ሳይሆን፥ የሀገራችን ችግር ንቅንቅ ለማለት ባለመቻሉ ነው፡፡

የትግል ዓላማዎቻችንን በሚገባ አውቀንና ተረድተን፥ ወዳጅና ጠላትን በየፈርጁ ለይተን መጓዝ፥ ለመፍትሔ ፍለጋው ጥረት በብርቱ ይረዳናል፡፡ ለዚህ ጥረት ስኬታማነት ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ የሚያርፈው በቅድሚያ በሁለት የኅብረተስብ ክፍሎች ላይ ብቻ መሆኑ ሁሉም ይገነዘበዋል፡፡ እነርሱም፥ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሀገሪቱ ምሁራን ናቸው፡፡ ወደዱትም ጠሉት እነኝህ ሁለት የኅብረተሰብ ክፍሎች፥ ሀገሪቱን አሁን ከገባችበት የጥፋት አዘቅት ለማውጣት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ሊያውቁት ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉጉት የሚጠብቀው ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ምሁራንና የተቃዋሚው ጎራ እስካሁን በሚጠበቅባቸው ደረጃ ተገናኝተው፥ ተወያይተውና ተግባብተው ብሄራዊ መፍትሄ የሚገኝበትን የጋራ መድረክ ከፍተው ለመወያየት የጣሩበት አጋጣሚ ከነበረ ለማስታወስ እንቸገራለን፡፡ ሁለቱም የአዋቂ አጥፊ ካልሆኑ በስተቀር፥ ኢትዮጵያን አሁን ካለችበት ችግር ለማዳን ብቻ ሳይሆን፥ ከወያኔ ዘረኛ ሥርዓት በኋላ ለሚከሰተው በሀገሪቱ የፖለቲካ መልከአምድር ላይ ወሳኝና ገንቢ ሚና አላቸው፡፡ ትግል ያለ ታጋይ ድርጅትና ያለ ምሁራን ተሳትፎ የትም አይደርስም፡፡ በመሆኑም፥ እነኝህ ክፍሎች ሊተባበሩና በጋራ ብሄራዊ አጀንዳ ዙሪያ አብረው ሊሰሩ የግድ ይሆናል፡፡

ለመሆኑ በአሁኑ ወቅት የሀገራችንና የሕዝባችን የቅድሚያ አጀንዳ ምንድን ነው? የምንፈልገውን አውቀን በቅደም ተከተል ተራ አስገብተን ልናራምደው የሚገባንን ሀገራዊ የትግል ሂደት እንዴት ማከናወን ይገባናል? ልናነጠራጥርበት የሚገባን የጋራ ዒላማችን በማን ላይ ነው? በርግጥ የተቃዋሚ ኃይሎች በጋራ የሚያነጣጥሩበት የጋራ ዒላማ አላቸውን? ወይስ ዒላማቸውን የሚያነጣጥሩት እርስ በዕርሳቸው ላይ ነው? እረ ለመሆኑ ሁሉን ያላሳተፈና ያላስተባበረ ትግል፥ ውጤት ያስገኛል በለው ያምናሉ? ይህን አምባገነን ዘረኛ ሥርዓት በአጭር ጊዜ ለመለወጥ የሚቻለውስ እንዴት ነው? እነኝህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እየጠየቁ ትክክለኛ መልሶችን አግኝቶ በተግባር መለውጥ መቻል ማለት፥ የምንፈልገውን አውቀን የቅድሚያ ተግባራችንን ተረደተን ወደሥራ ለመተርጎም ተዘጋጅተናል ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ ፥ ሁሉንም ለማሳተፍና ለማስተባበር የተሟላ ሁኔታን ፈጥረናል ማለት ነው፡፡ እናም ደግሞ፥ ሁሉም የሚመኘው የተቃዋሚ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ምሁራን ብሎም፥ መላው ኅብረተስብ የተረባረበበት ትግል የካሄዳል ማለት ነው፡፡ ይህን ማሳካት ከቻልን ደግሞ፥ በአጭር ጊዜ ውስጥ የትግሉን ውጤት ለማስመዝገብ የሚሳን አይሆንም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ መራራ ትግል በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት እንዲያስመዘግብ ከተፈለገ፥ የሚከተሉት ወሳኝ ርምጃዎች በግንባር ቀደምና በአስቸኳይ መፈፀም ይኖርባቸዋል ብለን እናምናለን፡፡

1) አሁንም እንደ ትላንቱ፥ ጠንካራ የተቃዋሚዎች ኅብረት ፈጥሮ በጋራ መታገል ወቅታዊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄና ፍላጎት መሆኑን አውቆ፥ በአስቸኳይ የተቃዋሚዎች ብርቱ ኅብረት መፈጠር አለበት። የእስካሁኑ ጥረት ወያኔን ሊያንበረክክ አልቻለም። ይህን እንደ ኮሶ የመረረ ሀቅ መቀበል፥ የታጋይ ድርጅቶች ኃላፊነትና ተግባር ነው። ይህን ሀቅ አለመቀበል ግን ራስን ከማታለል አልፎ፥ ትግሉንም ጻፍንታም ማድረግ ይሆናል።

2) እስካሁን የተደረገው ጥረት ሁሉ ተፈላጊውን የሕዝብ ውጤት ሊያስገኝ አላስቻለንም። በመሆኑም፥ ውጤት ሊያስገኝና ድልን ሊያመጣልን በሚችለው የተግባር አፈጻጸም ላይ ማተኮር ይኖርብናል።

3) በብሔራዊ አጀንዳ ላይ የተመሠረተ አዲስ የትግል ስልትና ስትራተጅ መንደፍ፥ ተገቢና አጣዳፊ መሆኑን በማመን ይህን ማድረግ ይዋል ይደር የሚባል አይደለም። በመሆኑም፥ ሁሉንም የኅብረተስብ ክፍል ወደትግል መድረክ ሊያሰባስብና ሊያሳትፍ የሚችል አዲስ የጋራ ራዕይን ያገናዘበ የትግል ስልት መነደፍ አለበት።

4) የኢትዮጵያን የትግል ሂደትም ሆነ ውጤት የተሳካ ለማድረግ ከታመነበት፥ በተቃዋሚው ጎራ የሚታየው የእርስ በእርስ መጎነታተልና መነቃቀፍ በአስቸኳይ መቆም አለበት። ይህ ድርጊት እስካሁን ትግሉን ከመጉዳት በስተቀር ያመጣው አዎንታዊ አስተዋጽዖ የለም። በአንፃሩ ግን ወያኔን ጠቅሞታል ለማለት ይቻላል። ሁሉም ድርጅቶች ሊገነዘቡት የሚገባቸው ጉዳይ ቢኖር፥ የሀገራችንን ችግር ለመፍታት የሚቻለው በአንድ ወይም በተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን፥ በሁሉም ድርጅቶች የተባበረ ኃይል መሆኑን ነው። ወጣም ወረደ፥ ወያኔን ማንበርከክ የሚቻለው፥ ሁሉንም ባካተተ ትግል ብቻ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። የዚህ ዓይነት የትግል ሂደት፥ ሁለት ዓበይት ጥቅሞች ይኖሩታል ማለት እንችላለን። አንደኛው፥ሁሉም ከተባበረ የትግሉን ጎዞ ሊያሳጥረው ይችላል። ሁለተኛው ደግሞ ከኀልፈት ወያኔ በኋላ በሚደረገው የመሸጋገሪያ ጊዜና ከዚያም ባሻገር በሚደረገው የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ሁሉንም ሊያሳትፍ የሚችል አውደ-( የ) ፖለቲካ መድረክ ሊፈጠር ይችላል።

5) የትግሉን ደካማና ጠንካራ ጎን በመገምገም፥ አዳዲስ የአሰራርና የግንኙነት፥ የአመለካከትና ያካሄድ ለውጥ ማድረግና ወደ አዲስ የትግል ምዕራፍ ሊያሸጋግር የሚያስችል ዘዴ ማዘጋጀት ለውጤት ማስገኛ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ያደርጋል። ሁሉንም ዓይነት የትግል ስልት መጠቀም፥ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፥ ሁኔታዎቹ የሚያስገድዱት ዕውነታ ነው። ይህን አለመገንዘብ በአሮጌ በሬ እንደማረስ ይቆጠራል። ወቅቱ የሚጠይቀውን የሕዝብ ፍላጎት ቀድሞ ካልተገነዘቡ፥ " የሞተ ፈረስ ጋላቢ፥ የደረቀ ወንዝ ተሻጋሪ" የሚል ቅፅል ያሰጣል።

6) ሀገር ወዳድ የሆኑት ምሁራን ሁሉ በትግሉ የሚሳተፉበትን ማድረግ ማዘጋጀት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ወሳኝም ነው። እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ምሁራን የሚፈለገውን ያህል ተሳትፈዋል ማለት የሚቻል አይመስለንም።

7) የወያኔን ባኅርይና ሥነልቦና ፥ የአሰራር ስልትና ድርጅታዊ ማንነት ፥ የመረጃ መዋቅሮቹንም ጠንቅቆ ማወቅ ከወያኔ ተንኮልና ሰርጎ ገቦች ያድናል።

8) በአማራጭ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያውቀው የሚገባ አንድ የጋራ የዜና ማዕከል ፈጥሮ፥ በጋራ ትብብር የሚካሄድ የራዲዮ ስርጭት ፕሮግራም ማካሄድ ወቅታዊና ወሳኝ ነው። ይህ የዜና ማዕከል ዓላማና ተግባር በወያኔ ፕሮፓጋንዳ የሚደነቆረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ አማራጭና ትክክለኛ የሆነ መረጃና ዜና እንዲያገኝ ከማገልገሉም በቀር፥ በትግሉ ሂደት አቅጣጫና መርህ በመስጠት ደረጃ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ይኖረዋል። የወያኔንም የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ለማጋለጥ የተሻለ ዕድል ይኖረዋል።

9) ሀገራዊ ትግል በበጎ ፈቃድና ምኞት፥ ወይም በአምባገነኖች ርኅራኄና ልግስና፥ ወይም ደግሞ በባዕዳን ውሳኔና ትዕዛዝ የሚካሄድ አይደለም። በሳል መሪዎችን ፥ ወሳኝ ርምጃን ፥ ቆራጥ ውሳኔን፥ ቀጣይና ያልታከተ፥ ያላወላወለና ያልተበገረ አመራር ሰጭነትን ይጠይቃል። አስፈላጊ መሥዋዕትንም መክፈል ከጠየቀ፥ ለዚሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል። "ያለ ደም ስርዕየት የለም" እንዲሉ፥ ያለ መሥዋዕት፥ ትግል ግቡን የማይመታ መሆኑን በቅድሚያ ተገንዝቦ የሚመጣውን መሥዋዕት ለመቀበል ፈቃደኛ ሆኖ መዘጋጀት ያስፈልጋል። "በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ" የሚባል ነገር በትግል ሂደት አይሰራም። እያንዳንዱ ዜጋ የየበኩሉን እንደ የአቅሙ መሥዋዕት መክፈል አለበት። እስካሁን በታሪካችን እንደታየው ከሆነ፥ ጀግኖች እየተሰው፥ ደፋሮቹ በግንባር ቀደም እየተደፉ፥ ያሞራ ሲሳይ ሆነው ነው የቀሩት። ለዚህ ይመስለናል፥ የታሪክ ታዛቢዎቹ፥

> " አንድ አንድ ጠብደል አለ ጎተና አሳማሪ፥
> ሲሄዱ በኋላ ሲመለሱ መሪ" ብለው እንጉርጉሮ የሚያሰሙት።

10) ይህም ተባለ ያ፥ ዞሮ ዞሮ ኢትዮጵያ አሁን ከወደቀችበት ፈታኝ ጊዜ እንድትወጣ ከተፈለገ ፥ የሁሉንም ዜጎቿ ትብብርና ተሳትፎ የሚጠይቅ የኅብረት ትግል ማካሄድ ወሳኝ ነው። በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ፥ "የጥሎ ማለፍ" ጨዋታ ለማንም እንዳልጠቀመ፥ መገንዘብ ያስፈልጋል። በዕርግጥ የወያኔ አገዛዝ መወገድ አለበት።ይህ ደግሞ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው፥ የተቃዋሚው ጎራ እራሱን አስተባብሮና ጠንካራ ኅብረት መሥርቶና መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተባብሮና በሀገራዊ አጀንዳ ዙሪያ ተሰልፎ ሲታገል ብቻ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ከልብ ከታሰበበት ከባድ አይሆንም።